በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 216299

ቀን ግንቦት 25 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡ 1ኛ. አቶ አበበ እንሰተ

2ኛ. አቶ ደረጀ እንሰተ

3ኛ. ወ/ሮ ተዋበች እንሰተ } አልቀረቡም፡

4ኛ. አቶ ሽመልስ እንሰተ

ተጠሪ፡ አቶ ኃይሉ ቦሬሳ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የን/ስ/ላ/ምድብ በኮ.መ.ቁ 176966 በ3/2/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 277758 በ29/2/14ዓ.ም በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት በ8/3/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በፍ/ቤቱ በመ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍርድ ቤቱ ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ህ/ቁ 998 መሰረት እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ወይም ውርስ አጣሪ ሪፖርት የጸደቀበትን የፍርድ ቤት ውሳኔ ለማሰረዝ የሚቀርብ ክስ መቅረብ የሚኖርበት በራሱ ሪፖርቱ በጸደቀበት መዝገብ እንጂ በአዲስ መዝገብ መሆን ስለሌለበት አመልካቾች እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት የውርስ አጣሪ ሪፖርት በጸደቀበት መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን የማቅረብ መብት ተጠብቆላቸዋል በማለት በሰጠው ትእዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ትእዛዝ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ብይን ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ትእዛዝ እና ብይን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 የተሰጠው ፍርድ የሚፈጸም ከሆነ ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያ ማቅረብ እንደሚቻል ደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኮ.መ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም ያጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት የሚፈጸም ባለመሆኑ ከላይ ከተገለጸው ድንጋጌ አንጻር አመልካቾች በማይፈጸም ፍርድ መቃወሚያ ልናቀርብ የማንችል ሲሆን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍርድ ያጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት የማይፈጸም መሆኑን መረዳት ሲገባው አመልካቾች እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁት የውርስ አጣሪ ሪፖርት በጸደቀበት መዝገብ ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት ተጠብቆላቸው መዝገቡ ተዘግቷል በማለት የሰጠው ትእዛዝም ሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዚሁ ትእዛዝ ላይ የቀረበውን ይግባኝ በመሰረዝ የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 45905(ቅጽ 11) በፍ/ቤቱ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማስረጃነት የሚያገለግል ሆኖ ይህን የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን በማስረጃነት ተጠቅሞ የድርሻ ክፍፍል ዳኝነት ለመጠየቅ የሚያገለግል እንጂ በቀጥታ ውሳኔው ለአፈጻጸም ችሎት የሚቀርብ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበት አይደለም ሲል ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር እንዲሁም የኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ከደነገገው አንጻር የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ ክርክሩ በከፈትነው አዲሱ የመ.ቁ 176966 ላይ እንዲቀጥል ውሳኔ እንዲሰጥልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ውርስ ተጣርቶ በጸደቀበት መዝገብ ላይ እንጂ እንደ አዲስ ክስ ማቅረብ አይቻልም ተብሎ የዳኝነት ጥያቄያቸው ውድቅ መደረጉ በሰ.መ.ቁ 45905 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ27/4/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በ17/6/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ እና ብይን ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በ30/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እና ብይን እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ እና ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ.መ.ቁ 45905 (ቅጽ 11) በመጥቀስ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በዚሁ በተጠቀሰው የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ላይ የነበረው ክርክር በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርሱ ተጣርቶ ቀርቦ በፍ/ቤቱ ከጸደቀ በኂላ ይህን የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በመያዝ የውርስ ሀብት ክፍፍል ድርሻ ክስ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ክርክር ተካሂዶ የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔው መብታችንን ይነካል ያሉ አመልካች ፍርድ ይታረምልን ሲሉ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ያቀረቡትን የፍርድ መቃወም አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ ውርስ የተጣራው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተሾመው የውርስ አጣሪ ስለሆነ የውርስ ማጣራት ሪፖርቱ ደግሞ አመልካችን የማያውቃቸው መሆኑን በመግለጽ የፍርድ መቃወሚያው ሪፖርቱን ላጸደቀው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሚቀርብ በቀር የውርስ ሀብት ክፍፍል ውሳኔ ለሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው በመቅረቱ ምክንያት አመልካች እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረው ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች አቤቱታ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358ን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ሲሆን የአመልካችን መብት ይነካል የተባለው እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የተሰጠው በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመሆኑ አመልካች ከማስረጃነት ዋጋ ውጪ ሌላ ዋጋ የሌለውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ሊቃወም የሚችልበት አግባብ የለም በማለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናውን ውሳኔ በመሻር አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉት በውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ላይ ውሳኔ ለሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ላጸደቀው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይደለም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀብሎና የግራቀኙን ቀሪውን ሁሉን ክርክር በመመርመር ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በመመለስ ውሳኔ የሰጠበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 176966 በሆነው መዝገብ ላይ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በመ.ቁ 105883 በ29/6/08ዓ.ም በፍ/ቤቱ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲሰረዝልን የሚል ሲሆን ይህ አቤቱታ ከላይ የተገለጸው በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የታየውን ከውርስ አጣሪ ሪፖርት መጽደቅ እና ይህንኑ ሪፖርት መሰረት አድርጎ የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ክስ መቅረብ እና በዚሁ ላይም የውርስ ሀብት ድርሻ ክፍፍል ውሳኔን ሂደት ያለፈ ሳይሆን በፍ/ቤት ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይሰረዝልን የሚል ይዘት ብቻ ያለው በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 45905 ከላይ በተገለጸው መልኩ የተሰጠው ውሳኔ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በፍ/ቤት ጸድቆ የነበረ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ይሰረዝልን የሚል አቤቱታ በዛው ሪፖርቱ በጸደቀበት መዝገብ ላይ ሊቀርብ የሚገባው እንጂ ሪፖርቱ ከጸደቀበት መዝገብ ውጪ በሌላ የክስ መዝገብ ይስተናገድ የሚባልበት የህግ መሰረት አለመኖሩን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በመሆኑም የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትእዛዝ እና ብይን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የን/ስ/ላ/ምድብ በኮ.መ.ቁ 176966 በ3/2/14ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 277758 በ29/2/14ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም